የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፶፮
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year - No. 56
ADDIS ABABA 24th July, 2014

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፭/፪ሺ፮ ዓ.ም

ለመጀመሪያው ዙር የሞጆ-ሃዋሳ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……………………ገጽ ፯ሺ፬፻፷፰

CONTENTS

Proclamation No-855/2014

Export-Import Bank of Korea Loan Agreement to Provide Loan for Financing the First Phase Modjo-Hawassa Road Project Ratification Proclamation……………………page 7468

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፭/፪ሺ፮

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለመጀመሪያው ዙር የሞጆ-ሀዋሳ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፩፻ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /አንድ መቶ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.አ.አ. ሜይ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፬ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፱ ቀን ፪ሺ፮ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO.855/2014

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT-IMPORT BANK OF KOREA

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of Korea stipulating that the Export-Import Bank of Korea provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan in amount equivalent to USD 100,000,000 /One Hundred Million United states Dollar/ for Financing the First phase Modjo-Hawassa Road Project was signed on the 22nd day of May, 2014;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 26th day of June, 2014;

NOW, THERE FORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለመጀመሪያው ዙር የሞጆ-ሀዋሳ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፭/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮሪያ ኤክስፖርት- ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.አ.አ. ሜይ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፬ የተፈረመው ቁጥር ETH-2 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /አንድ መቶ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as the "Export-Import Bank of Korea Loan Agreement to provide Loan for Financing the First Phase Modjo-Hawassa Road project Ratification proclamation No.855/2014".

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement No.ETH-2 signed in on the 22nd day of May 2014 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of Korea is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of USD 100,000,000 /One Hundred Million United states Dollars/ in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This proclamation shall enter in to force on the date of publication in the federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 24th day of July, 2014**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት